# ይድረስ ለግንቦት 7
# አባላትና ደጋፊዎች

ከቀመሩ ደሳለኝ

ወያኔ/ሕወሓት የትግራይ ነፃ አውጭ ገና ከጥንስሱና ከጅምሩ፣የኢትዮጵና የሕዝቧ ዋና ጠላትነት ገሃድ ሆኖ የታያቸውና ያወቁ አገር ወዳድ ወገኖች ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሰጡት አስተያየትና ምክር፣የኢትዮጵያ ሕዝብ በብልጠት ቶሎ ተዘጋጅቶ የደርግን መንግሥት በአንድ እጁ በሌላው ደግሞ እነዚህን ፀረ_አገርና ሕዝብ ወያኔ_ ባንዳዎች ሁለቱንም በአንድ ወቅት በግራና በቀኝ መምታትና ማስወገድ አለበት እየተባለ ብዙ ተነግሮና ተጭሆ ነበር ። ይህ የማይረሳ ሃቅ ነው። ነገር ግን ሰሚና ልብ ሊያደርገውና በወቅቱ ሊከላከለው ባለመቻሉ ዛሬ አገር፣ ሕዝብና ሰንደቅ ዓላማ ተደፍረውና እየተዋረዱ በስቃይና በችግር በነዚህ አረመኔ ዘረኛና ፋሽስት፣ማፊያ ወያኔ ባንዳዎች በሕገ ወጥ ሥርዓት ሥር ወድቀው እየተገዙ ይገኛሉ።

በዚህ ሥርዓት ግልገል ባንዳዎች በየቦታውና በየአቅጣጫ ተቃዋሚዎች በመስለ እየተቀፈቀፉ በሕዝብ መሀል በመግባት በዝተውና ተባዝተው ብዥታ በመፍር እያወናበዱ አገርና ወገንን ሲጐዱና ሲበድሉ በአንጻሩ ደግሞ ፣ በቀጥታም ሆነ በሥውር እያደነቁና እያሞገሱ ርዕዮተ ዓለሙንና ሥርዓቱትን ተቀብለው ፀረ_ ኅብረተሰብ ወያኔንን እየጠቀሙ  ይህው 22 ዓመታት አለፈ።

የትግል ተቀዳሚው ተግባር ጠላትን መለየትና ማወቅ እንደተባለው ሁሉ ግንቦት 7 ከመፈጠሩ ዋዜማ የእነ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌና ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ማንነትና ተግባራቸው በብዙ አገር ወዳድ የታወቀና ግንዛቤ ስለነበረ እንደ አለፈውም ጊዜ የነዚህን ስውር ባንዳዎች ጉዳይ በግልጽና በይፋ ማሳሰቢያ ጭምር ተነግሮ ነበር ዳሩ ግን እንደገና ሰሚ ሊያገኝ አልቻለም።

የዛሬዎቹ የግንቦት 7 መስራችና መሪዎች የትናንት የወያኔ ተባባሪና አገልሎት ሰጭ፣ የዛሬ የወያኔ ተቃዋሚዎች፣ የስውር ባንዳዎች ፣ የኢትዮጵያና የሕዝቧ መሰሪ ጠላቶች ናቸው። አቶ አንዳርጋቸው ፣ ዶ/ር ብርሃኑና ከነዚህ ጀርባ ሌሎችን ጨምሮ ለወያኔ/ ሕወሓት መንገድ እየጠረጉ ከፍተኛ አገልግሎት ያደረጉ፣ የአገርቱን ምስጢር፣ልዩ ልዩ መረጃዎችንና ሰነዶችን ፣ መግቢያ መውጫውን የሰለሉና ያሳዩ፣ የመሩና ቤተመንግሥት ያስገቡ  ዛሬ በውጭ ያሉ ተቃዋሚ የሚባሉ ባንዳ ወያኔዎች ናቸው።ከወያኔ ቀፎ የወጣ ወይም ያመለጠ ሁሉ ወደ ብሔራዊ አንድነት ቀፎ ሊገባም ሆነ ማር ሊሰጥ አይችልም።የተመረዘ ነውና።

እነዚህ ሁለት ሰዎች የወያኔ ተቃዋሚ በመምሰል በሕዝብ ትግል ውስጥ በመግባት ቅንጅትን በዋናነት በወያኔ ለማስመታትና ብሎም እንድፈርስ ፣ እንድበታተን ያደረጉ ናቸው። ቅንጅትን የኢትዮጵያ ሕዝብ አምኖበት፣ ተስፋ ጥሎበት የተካፈለበትና የመረጠው ድርጅት፣ እንዲሁም ለብሔራዊ አንድነቱ ድምጹን ያሰማበት ፣ለሕዝባዊ መንግሥትነት የተቃረበበት ነበር።  ግንቦት ሰባት የመረጠበት ቀን ነበር። ይህ ግንቦት ሰባት የምርጫ ቀን ለኢትዮጵያኖች ታላቅ ቀን ሲሆን ፣በግንቦት 7 ድርጅት ዘርፎ መወሰዱ ሌላው ጸጸት በመሆኑ የኢትዮጵያ  ሕዝብን እጅግ ያስቆጣና ግንቦት 7 ድርጅትን ከወያኔ ለይቶ የማያየው ጠላቱ ነው። ግንቦት 7 ከዚህ ባሻገር ከአገር ጠላቶች ጋር የሚዋዋል፣የሚደራደር በሻቢያ ስር  የሚንቀሳንቀስ፣ ለሱዳን ወያኔ የሰጠውን መሬት የሚስማማበት መሆኑንና ለግብጽም የአባይ ወንዝን የሚሰጥና  ከነዚህ መሰል ጋር አብሮ እንደሚሰራ ተደርሶበታል። አገር አስገንጣይና ገንጣዮችን  በማሰባሰብ የሚዶልት ሸፍጠኛ ድርጅት ነው።

ግንቦት 7 ሰንኩል አሰተሳሰብና እኩይ ተግባር፣ ውሸትና ተንኮል፣ሥርዓት አልባ አመራሪ፣ አምባገነናዊ ባህሪ፣ የዲሲፕሊን መጓደል፣  ከአባላት ጋር መግባትና አክብሮት የጎደለው አመራር በመሆኑ ድርጅቱ ቀደም ሲል ለሁለት መከፈሉ የሚታወቅ ነው። "የእብድ ጭምት ከቀትር አያልፍም" እንደተባለው ወያኔዊ ባህሪያቸው እየፈጠጠ ወጣ። ይህን ልንሰራ ነው፣ይህ ድርጅት፣ ግለሰብ ተቀላቀለን እያሉ በየጊዜው ገንዘብ ከመሰብሰብ በስተቀር በአራት ዓመት ውስጥ ምንም ያልታየበት መካን ድርጅት ነው። ይህም በጉልህ የሚያሳየው የዚህን ድርጅት ደካማነትና ዋጋቢስነት ፣ ጉጅነት ያለው ለኢትዮጵያ የማይጠቅም መሆኑን ነው።

አሁን ሰሞኑን ደግሞ አቶ አንዳርጋቸው (በትናቸው) እንደልማዱ ሌላ የማጭበርበሪያ መወሸከቻ ከወደ አሥመራ በመገስገስ በኢሳት ትቪ ላይ ብቅ በማለት የውሸት ቡፋውን ሲለፍፍ ተሰማ። "አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያውጣል" ሆነና በለስ አልቀናውም፣ በተቃራኒው የግንቦት 7 ድርጅት ይበልጥ ዋጋ ቢስ መሆኑን ያሳየበት፣የውስጥ ገመናው ጉዱ እየጎላ ይፋ የወጣ ፣ አባላቱንም

አሳፈረ። ሕዝብም ተማረረ፣ ከእንግዲ ዝም አንልም አለ ። ለአባላትና ለደጋፊዎችም በግልጽ የዚህ ድርጅት ለአገር ፣ ለወገን ፋይዳ እንደሌለው ፍርጥም ብሎ የታየበትና በደንብ የተረዳችሁበት ጊዜ ነው። ልብና አስተዋይ ህሊና ካላችሁ።

የግንቦት 7 መሪዎች ማንነታቸውን በራሳቸ አንደባት በየአደባባዩ፣ በየቃለ ምልልሱና ገለጻው ላይ ዓይን ያወጣ መቀበጣጠ፣ ተንኰልና ውሸት በተሞላበት ፐሮፓጋንዳቸው አሳውቀዋል። ይህን የአቶ በትናቸውና ዶ/ር ብርሃኑ (አሚና) የሌሎችንም ንግግርና የዘወትር ስውር ሥራና ተግባር አስመልክቶ ብዙ አገር ወዳድ ተቋርቋሪዎች የነዚህ ግለሰቦች ሸፍጥና ስውር ተግባር፣ መሰሪ አካሄድ እጅግ አደጋኛነት የአሳሰባቸውና ያስጨነቃቸው ከመሆኑ ጋር፣ የታዘቡትንና የተሰማቸውን ገምግመው ለአገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያውቀው፣ ይረዳው ዘንድ የተለያዩ የጻፉና የተነገሩ መረጃዎችን በሰፊው በየድህረ ገጾችና በብዙ ሬድዮኖች፣ ዩቲዩብ ላይ ይገኛሉ ያንብቡት። *መረጃዎች(1_ አንዳርጋቸው ከኢሳያስ ጉያ፣ ነፃነት ወይስ ባርነት_ ከቦጋለ ካሳዬ ፣ 2_ማስታገሻ መርፌ ውጋው_ ከአንበሳ ይብራ ፣ 3_ ዝም ማለት ወንጀል ነው_ ከአንዱ ዓለም ተፈራ፣ 4_ ሲ አይ ኤ ልጆቹና የልጅልጆቹ ሴራ በኢትዮጵያ_ ከጌታቸው ረዳ_ የኢትዮጵያ ሰማይ ድረ ገጽ ፣ 5_ይድረስ ለአንዳርጋቸው ፅጌ ጥብቅና ለሻቢያ _ከአንበሳ ይብራ ፣ 6_ኢትዮጵያዊነት ሬድዮ ፣ዩቲዩብ ይመልከቱ)*። የአገር ጉዳይ ነው አንብቡት፣ አገናዝቡት ።

ግንቦት 7 የተቋቋመው የወያኔን የዘረኛና ፋሽስት መንግሥት፣ርዕዮተ ዓለምና ሥርዓት ሁሉ ለማራመድና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የኢትዮጵያን አገራዊ አህዳዊ ሉዓላዊነት በተጻረረ ሁኔታ የሕዝቧን አንድነት፣ ኅብረቷን፣የአገርን ክብርና ታሪክ በማንቋሸሽና በማራከስ ባንዳዎች የሚጠቀሙበትን ፐሮፓጋንዳና አቋም ፀረ_ኢትዮጵያ፣ ፀረ_ብሔራዊ ለመሆኑ ግልጽና የታወቀ ነው።በዚህ ድርጅት ጀርባ የተሰባሰቡትና የተካተቱት አባላት፣ ተባባሪ ድርጅቶች ሁሉ የወያኔ የተቃዋሚነት ስም ይኑራቸው እንጂ፣ ሆዳምና ሌባ፣ አፍራሽና ተገንጣይ፣ ባንዳና የባንዳ ልጆች የአገር ጠላቶች ናቸው።

ስለዚህ የግንቦት 7 አባላትና ደጋፊ አገር ወዳድ ሁሉ ይህን ድርጅት በምስረታው፣ በማደራጀቱ፣ እስከ አሁን ስዓት ድረስ የተከተላችሁ፣የምታገለግሉ፣በአሳብ፣በሞራልና በገንዘብ እየረዳችሁ ያላችሁት ኢትዮጵያ አገራችን ከወደቀችበት ችግር ከወያኔ አረመኔያዊ ሥርዓትና ጥፋት እናድናለን ኢትዮጵያን ይህ ድርጅት ይታደጋታል ብላችሁ በበጎ አስተሳሰብና ቅንነት ነው ብየ እገምታለሁ።ነገር ግን ከዚህ በላይ ባለው መረጃና በአለፉት አራት ዓመታት መሪወቻችሁ የሰሩት፣የተናገሩት ሁሉ ውሸት፣ ሸፍጥና ሃሰት ነው።ዶ/ር ብርሃኑ አንዳርጋቸው ምን ሰሩ? ምን ተናገሩ ? እነማን ናቸው ትናንት? ዛሬስ? ብለችሁ እውነትን የምትረዱበት አሁን ነው።እስከ ሚያንገሸግሻችሁ የሰማችሁ መሰለኝ። ይህ ድርጅት ሲቋቋም ጀምሮ ከወያኔ ያልተለየ፣ የወያኔ አምሳያ ግልገል ባንዳዎች የፈጠሩት ለኢትዮጵያና ሕዝቧ ምንም ፋይዳ የሌለው ነው።ስለሆነምይህ ድርጅት ከወያኔ የማያንስ ሸፍጥና ተንኰል በአገራችን ሕልውና ላይ ከፉ መዘዝ የሚያስከትል እየስበኩና እያሰራጩ ነው።የግንቦት 7 መሪዎች በውሸት ላይ ሰለተመሰረቱ የሚተጣጠፍ አቋማቸው በምላሳቸው ወለምታ ለማንም ግልጽ እየሆነ ያለ ሃቅ ነው። ከእንግዲህ ይህን ድርጅት ተከትሎ መሄድና መርዳት አበው እንደሚሉት "እባብን በረደው ብሎ እጉያ እንደ መያዝ"ይሆንና መርዙ ለሁላችንም ይተርፋል። አገርን መጉዳት፣መሸጥ ፣ ማጥፋት ሕዝብን መበደል፣ ትልቅ ወንጀል በሕግ የሚያስጠይቅና ከፍተኛ ቅጣትን የሚያስከትል ነው።የተደጋገመ ስህተት ውጤቱ ውድቀት፣ ትርፉ ኪሳራና መጥፋትም ነው።

ሰለዚህ አገራችሁንና ሕዝባችሁን የምትወዱና የምታስቡ ከሆናችሁ ንቁና በአስቸኳይ ከድርጅቱ ውጡ።ያለበለዚያ እናት ኢትዮጵያ የምትፋረዳችሁ መሆኑን በጥብቅ እናሳውቃለን ።

ምንጊዜም ኢትዮጵያ !

ሕዝብ አሸናፊ ኃይል ነው !